# የማታውቅበትን የሰው . . .

ከበልጅግ ዓሊ

ቢሆንማ

ጨለማው ተገፎ ፣ ሌቱ እስቲነጋ
ያስከፍላል እንጂ ዘርፍ ብዙ ዋጋ
ምንም ጊዜ ቢሆን ነበረ ባልከፋ
ዶማን ዶማ ማለት አካፋን አካፋ።

ነሐሴ - 1998 ዓ.ም.
የሕሊና ፀዳል - አየለ አሻግሬ

አንድ የማውቀው ግለሰብ በቅርብ ቀን ወደ ቤቴ ይመጣና ጨዋታ ይጀምራል። በፈገግታው አዲስ ነገር ሊነግረኝ እንደፈለገ ገብቶኝ፡ -
"ምን አዲስ ነገር አለ ?" ብዬ ጠየቅኩት።
"ያንን ሻዕብያ! ጉድ አደረጉት።"
"የቱን?"
"ያ ወዳጅህን!።"
"ደግሞ የቱ ነው ወዳጄ?"
"ተስፋዬ ገብረአብ ነዋ።
"ደግሞ ከመቼ ጀምሮ ነው እኔና እሱ ወዳጆች የሆነው?"
"አንድ ሰሞን የሱን መጽሐፉን ታቅፈህ እሹሩሩ ስትዞር አልነበረም እንዴ?"
መጽሐፉን ያነበብኩለት ደራሲ ሁሉ ጓደኛዬ ከሆነማ ይሁንና ብዬ ጨዋታውን በመቀጠል፡-
"ለመሆኑ እሱ ሻዕብያ መሆኑን በምን አወቅህ?"
" ከንፈ ነገረኝ።"
" ከንፈ የቱ?"
" የወያኔ የስለላ ሀላፊ የነበረው"
"አትቀልድ እሱ ሞቶ የለም እንዴ?"አልኩት
" ከመሞቱ በፊት ደውሎ ለእኔ ብቻ ነው የነገረኝ። ከፈለክ ጠይቀው።"
"በህይወት የሌለን ሰው? እንዴት ነው የምጠይቀው?"
"አንድ ቀን መፃፍ ከቻልኩ ጥሩ መድብል ይወጣዋል። መጽሐፍ ሽጬ አተርፍበታለሁ።ጥሩ ኖቭል ሳይወጣው አይቀርም።" ጥያቄዬን ያልሰማ በመመሰል ቀጠለ ።
" የእኔ ሲሆን በጥያቄ ታጣድፈኝአለህ ። እሱ ሲሆን ግን ታምነዋለህ።እሱ ወያኔ ስለነበር ነው የሚከበረው? የሚጽፈው ፣ የሚወራው ሁሉ እውነት ነው ተብሎ የሚታመነው?" አለኝ ንዴቱን በሚገልጽ ሁኔታ።
መልስ መስጠት አልፈለኩም። ጭውውቱን ወደ ሌላ ወሰድኩት።
" ዛሬ ምነው የተስፍሽ ነገር አንጨረጨረህ? ደግሞ ምን ፃፈ?"
" አልሰማህም እንዴ ፓልቶክ ላይ የሰጠውን ቃለመጠይቅ? ጉደኛ ሰው ነው። ብሎ እንደገና አማራንና ኦሮሞን ለማጋጨት ሲጥር እጅ ከፍንጅ ያዙት እኮ!።"
" አልገባኝም። ምን ማለትህ ነው?"
"ስማውና ትረዳዋለህ።"

ከፓልቶክ የቀዳውን ልኮልኝ መስማት ጀመርኩ። ተስፋዬ ከዚህ በፊት ቃለመጠይቅ እዚሁ ክፍል ሲሰጥ ተከታትየው አውቃለሁ። በሚያስፈራ ሁኔታ ደጋፊዎቹ ሁሉ ተቃዋሚዎቹ ሆነው ማግኘቴ አስደነቀኝ። ቃለ መጠይቁን እየስማሁ ተስፍሽ ጉድሽ ፈላ! ። ድሮ በወጣትነታችን እንዳየነው ፊልም ሬድ ኢንድያን እንደደረሰበትና መግቢያ እንዳጣ ቴክስ

ለማምለጥ ያደረገው ሙከራ ሁሉ ይከሽፍ ጀመር። ስዩ ፣ አብርሃ በላይ ፣ ኢትዮ ሚዲያ ፣ ኢሕአፓ ፣ ኢያሱ . . . ዛሬ ሁሉም አላዋጡም። በአውላላ ሜዳ ላይ እንደቆመች ገጣባ መጋዣ ተነጥሎ ሲቀር ታየኝ፣ አሳዘነኝም!

ተስፋዬ ሳያውቀው ያስጨበጭብልኛል ብሎ ያሰበው የነበረው ምስጢር ፈረንጅ እንደሚለው (Pandora's Box) ሆነበት። ተስፍሽ በዚሁ የፓልቶክ ክፍል ከዓለም አንደኛ እንዳልተባለ ዛሬ ውራ ሆኖ መንተባተብ ጀመረ። የተናገረው ያልታሰበ ችግር ይዞ ብቅ አለ። እስቲ ላልተከታተላችሁት ነገሩን ላብራራው።

ተስፋዬ "ለመናገር ስለማልፈልግ ነው እንጂ እነ ስዩ ለእኔ የነገሩኝ ብዙ ነገር አለ በሚል ይጀምራል።" ተስፍሽ አራዳው፣ እራሱን ገና ብዙ ምሥጢር አዋቂ በማስመሰል በሚያደርገው ሙከራ፣ ሳያውቀው ጉድ ሆነ። ወሬ መስማት ሱስ የሆነበት የፓልቶክ እድምተኛ፣ ሥጋ እንደተራበ አውሬ አሰፍስፎ ሙዳ ሙዳ የወሬ ጮማ (እራሳቸው ወያኔዎችም ጭምር)፣ ብልት ያለው ወሬ ለመግመጥ ጓጉተው ነበር። እንደ ምራቅ አስውጦ አልናገርም ማለት ምን ችግር ሊያስከትል እንደሚችል ተስፋዬ በውል ያጤነው አልመሰለኝም። ከዛ በኋላ ያስተካከለ እየመሰለው በስህተት ላይ ስህተት እያደለበ ነጎደ።

ከስህተቱ ሁሉ ብዘውን ታዳሚ ያሳሰበው በሕይወት የሌሉት ኢትዮጵያዊ የጦቢያና የአፄ ምኒልክ ታሪክ ደራሲ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ጉዳይ ነበር። እጅ ከፍንጅም የተያዘው እዚሁ ላይ ነው። ተስፋዬ እንዲናገር በተወጠረ ጊዜ እሱ ሃላፊነት የሚሰማው ጸሐፊ በመሆኑ፣_እነ ስዩ የተነገሩት ምስጢሮችን ቢናገር አስከፊ ሁኔታ እንደሚፈጠር በማሰብ ምንም ቢሆን ምስጢሮቹን እንደማያወጣ ገልጾ፣ ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ሃላፊነት የማይሰማቸው ጸሐፊዎች እንደነበሩ፣ ከእነርሱም ውስጥ የአፄ ምኒልክ ታሪክ የጻፉት አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ አንዱ ናቸው በማለት በአፄ ሚኒሊክ ታሪክ ላይ የፃፉትን በመጥቀስ፡ -

> አይሆንም እንጂ ተሆነማ
> ተመጋዞ ይሻላል ጉልማ ።

ብለው የፃፉት "ተመጋዞ" የሚለው ትግሬን ለመስደብ ሲሆን "ጉልማ" ደግሞ የኦሮሞ ስም ነውና ኦሮሞን ለመናቅ የሸዋ ሰው የተጠቀመበት በመሆኑ መጻፍ አልነበረባቸውም በሚል ንግግር አደረገ። ነገር ግን አማርኛ ጠንቅቆ ለሚያውቅ ሰው ደግሞ የተስፋዬ ስህተት (ተንኮል) ብዙዎቹ ታዳሚዎች እንዳሰቡት ጉልህ ሆኖ ነው የሚታየው፡፡ በመጀመሪያ አንባቢያን ፍርዱን እንድትሰጡ መጽሐፉ ላይ ያለውን እንዳለ እንመልከተው።

> ገጽ 50
>
> አጤ ምኒልክ ያን ሁሉ ሰልፍ በፈረስ ሁነው ዳር እስከዳር እየቃኙ አዩ አዩና **ከልበዎ** በደረሰ ጊዜ ቀኝና ግራውን በዘንግ እያሳዩ በዚህም ቢመጣ በዚህም ቢመጣ ውሎህ እንዲህ ነው አሉና ለሠራዊቱ ነገሩ። የዛን ጊዜ አውጥተው ባይናገሩትም ትግሬ ቢመጣ እንዲህ ሆነህ ተሰልፈህ በስናድርና በመድፍ አቅልጠው፣ በፈረስ አደባየው **ማለትዎ** ለሁሉ ገባው ። የመከዳተዎ ነገር ታወቀ። ከዚህ ላይ አቅራሪ ተነሳና
>
> አይሆንም እንጂ ተሆነማ
> ተመጋዞ ይሻላል ጉልማ ።

ብሎ አቅራራ ። ( በቀይ የተፃፈው አፄ ምኒልክን በአንቱታ እንዴት ይፃፍ እንደነበር የሚያስረዳ ነው)

ጥያቄው "መጋዞ" ምንድነው ? "ጉልማ" ማለትስ ተስፋዬ እንደጠቀሰው የኦሮሞ ስም ስለሆነ ኦሮሞን ለመናቅ ነው ወይ? የሚለው ነው። በክፍሉ አንድ አማርኛ በቅጡ የሚያውቅ ታዳሚ ወዲያው "መጋዞ" ማለት እርቦ መስፈር፣ መገበር ፣ ጭሰኛ መሆን፣ መሬት ተጋዝቶ ማረስ ማለት ሲሆን፣ "ጉልማ" ደግሞ የግል ይዞታ፣ ባለቤትነትን፣ ባለንብረት መሆን፣ አለመገበር የሚያመለክት እንጂ፣ ከዘር ጋር ተያይዞ የተነገረ አለመሆኑን ጠቅሶ ማብራሪያ ሰጥቶ ነበር። እንግዲህ

አንባቢያን እንደምትመለከቱት አቅራሪው በወቅቱ ከተለመደው ከመገበር(ከጭሰኝነት) ጋር በተያያዘ እንጂ ተስፋዬ እንዳለው ዘርን የተመለከተ አለመሆኑን ነው።

የተስፋዬን ቃለመጠይቅ ቅጂ የሰጠኝ ግለስብን ስለክንፈ የነገረኝ ምን ማለቱ እንደሆነ ስላልገባኝ እንደገና አነሳሁለት።
" ለመሆኑ ክንፈን እውነት ታውቀዋለህ?" ብዬ ጠየቅሁት።
" ስማ አትጃጃል ለመዋሸት ከፈለክ የሞተ ሰው ምስክርነት ጥራ የሚለውን የዘመኑን ፋሽን አታውቅም እንዴ ?። ብሎ አሳቀኝ። እውነቱን ነው ተስፋዬ ብዙውን ጊዜ መረጃ የሚያቀርበው የሞተ ሰው ነው።እንዲያውም ለእኔ ብቻ የነገረኝ የሚለውን ያበዛል። ብዙ አንባቢያን እንዲያውም የተስፋዬ ወሬ የሰፈር ሃሜት ነው የሚሉም አጋጥመውኛል።

"ግን ስለተስፋዬ ሻዕብያነት የነገርከኝ ትክክል አይደለም። የተሳሳተው ማንም ሰው ሊሳሳተው የሚችለው ነው እኮ። ደግሞ አካፋውን አካፋ ፣ ዶማውን ዶማ ማለቱን አትጥላው" አልኩት።

በጣም ስቆ " አካፋውን አካፋ ይበል ነው የምትለው? ታዲያ ምነው እንግዲህ አካፋውን አካፋ ዶማውን ዶማ ማለት ከፈለገ ተስፋዬ በቅርብ ሄዶ ስለጎበኘው ስለ ኤርትራው መሪ ኢሳያስ ይንገረና? ሰዋ ስለሚባለው የግፍ አምባ አልሰማም እንዴ? ኢሳያሳስ በጥፊ ስለሚመታቸው ሚኒስትሮችስ? ስለ አስመራው የፓለቲካ እስርቤትና ስቃይስ? የአማርኛ ዘፈን እንዳይሰሙ ስለተከለከሉት ወጣቶች፣ ስለሃይማኖት ነፃነት፣በኤርትራ የታሰሩ የአርበኞች ግንባር አባላትስ፣ እንዳኦሞ ስለአለው ለኢትዮጵያውያን ብቻ የተሠራ እሥር ቤት፣ . . . ወዘተ። በነገራችን ላይ ስለ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ የተናገረው ብዙ ሰው ነው እኮ የገረመው።"

" አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ እሱ ባላቸው መንገድ ላይወቀሱ ቢችሉም ሌላ ግን የሚወቀሱበት አለ" አልኩት። "እንዲያውም በአፄ ምኒልክ ወቅት ያሳዩትን የታላቅ ኢትዮጵያዊነት ጠባይ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የጣሊያን ባንዳ በመሆን አጥፍተውታል። በዚህ ሊወቀሱ ይገባል። ለምሳሌ እሳቸው የጻፉትንና ስለ እሳቸው የተጻፈውን እንመልከት" አልኩት።

አፈወርቅ ለሃገራቸው ከሠሩት ታላቅ ተግባር ውስጥ ራስ መኰንን የዛን ጊዜ ደጃዝማች ከውጫሌው ስምምነት በኋላ ወደ ኢጣሊያን ለጉብኝት የኢትዮጵያን መንግሥት ወክለው በሄዱበት ወቅት የተደረገላቸውን ታላቅ አቀባበል ከገለጹ በኋላ ሌለ የደረሰውን አሳሳቢ ጉዳይ አፈወርቅ የአፄ ምንሊክን በሚለው መፅሐፋቸው እንዲህ አስቀምጠውታል።

> ገጽ 70
>
> በዚህ ደስታ በዚህ ፍቅር መካከል ኢትዮጵያ በኢጣልያ መንግሥት ውስጥ ልትኖር ውል ተደረገ የሚል ወሬ በጋዜታ ላይ ተጣፈ። እቴጌና ጃንሆይ ጥበብ ተማር ብለው ኢጣሊያ አገር የሰደዱት አንድ አፈወርቅ የሚባል ትውልዱ ዘጌ የሆነ የኢትዮጵያ ልጅ ከዚያው ነበርና ይሄን ቃል ተጋዜታ አይቶ ለደጃች መኰንን በኢትዮጵያ ምነው እንዲህ ያለ ክፉ ነገር ተደረገባት ብሎ ነገረ። ደጃች መኰንን ቶሎ ብለው ያሄ ወሬ ይታረም አይሆንም ብለው ለኮንት አንቶኔሊ ተናገሩ። ወዲያው ደጃች መኰንንና ኮንት አንቶኔሊ በዚህ ነገር ተጣሉ።ያም የኢትዮጵያ ልዥ አፈወርቅ የጋዜታውን ቃል አውጥቶ ላገሩ ተቆርቊሮ ለደጃች መኰንን በተናገረበት ነገር ሮማ ላይ ግፍ ተሰራበት ። ኮንት አንቶኔሊ ፊት በገንዘብ ዝም እንዲል አባበለው የማይሆንለት በሆነ ጊዜ ግን አይቶ ባደባባይ ከፍ ዝቅ አድርጎ ሰደበው አዋረደው።

ይህ አፈወርቅ በምንሊክ ጊዜ ሲሆን በአፄ ኃይለስላሴ ወቅት ደግሞ የተለየ አቋም ይዘው ለኢጣሊያን ባንዳ ሆነው አገራቸውን ወግተዋል። አምሳሉ አክሊሉ 1976 ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ባዘጋጁት አጭር የኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ ታሪክ በሚለው ጽሁፍ ላይ

> ገጽ 118
>
> አፈወርቅ ገብረየሱስ ጠላት አገራችንን በወረረበት ጊዜ ለኢጣሊያን መንግሥት አድረው የፋሽሽቱ መንግሥት “ለሃገር ተወላጆች“ ከሚሰጠው ሹመት ትልቁን “አፈ ቄሳር“ የሚሰኘውን አግኝተው ነበር። በዚያ ጊዜ በአማርኛ ቋንቋ በየሳምንቱ እየታተመ የሚወጣው የጣሊያን መንግሥት ልሳን የሆነው “የቄሳር መንግሥት ማልእክተኛ“ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆነው ይሠሩ ነበር።
>
> . . . ሰውየው በሙሉ ልብ የጣሊያን ባንዳ ሆነው ስለነበር በዚያ በተሳለ አንደበታቸው ለኢጣሊያን መንግሥት መቆየት ያደርጉት የነበረው አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚታይ አልነበረም። ፋሽሽቶች በጦር ሕዝቡን የፈጁትን ያህል የአፈወርቅ ብእር የአርበኞችን ወኔ ለማዳከም ያልሞከረው መንገድ የለም ።

ይህንን ስንመለከት አፈወርቅ ልንወቅሳቸው የሚገባን ሌላ ጉልህ የሆነ ተግባራቸው እያለ ባልተጻፈው ላይ መሆኑ የሚያሳዝን ይሆናል ። ሥነ ጽሁፍ ለፋሽሽቶች መጠቀሚያ በሚሆንበት ጊዜ የሚመጣውን ጉዳት ከላይ ያየነው ሲሆን በቅርብ በወያኔም ዘመን ቢሆን ለብዙ ምስኪን ዜጎቻችን ሕይወት መጥፊያ መሆኑን በተስፋዬ ገብረአብ የተፃፈው "የቡርቃ ዝምታ" እንደ ምሳሌ የሚጠቀስ ነው።

ለማንኛውም ስለተስፋዬ ገብረአብ ብዙ በየሰፈሩ የሚያጨቃጭቅ ጉዳይ አለ። ብዙ ሰዎች ተስፋዬ ለሌሎች የሚጠቀምበትን የመጨረሻ አንጻ ቲዎሪን በተስፋዬ ላይ መጠቀም ይፈልጋሉ።ተስፋዬ ሻዕብያ ነው ወይስ እውነተኛ ሀቅን ዘጋቢ ? እነ ክንፈ ሞተዋልና እነ ስዬ እውነቱን ሊነግሩን ይገባል። ካልነገሩን ግን ተስፋዬን አምነን እንቀበል ይሆን ?

ታሪክም ቋንቋም ቢሆን ባለቤት አለው። ማንም ሲመቸው እየተነሳ የሚደለቅበት የዛር ዘፈን አይደለም። ቋንቋ ደግሞ በረዥም የማህበረ-ሰብ ሁለገብ ግንኙነት፣ እድገትና ውድቀት፣ እምነትና ፍልስፍና (እውቀት)፣ አመራረትና አኗኗር ወ.ዘ.ተ የዳበረና በማኅበረ-ሰብ ሕግ ሠፊ ተቀባይነት አግኝቶ በሁሉም ዘንድ በአወንታ ለዘመናት ሲሰራበት የኖረና የሚኖር ዓብይ የጋራ እሴት ነው።

የጨረባ ተዝካር ዓይነት፣ የቃላት የአሉባልታ ጋጋታ ላንድ ሰሞን **ተባለ እንዴ.......** ! ባዮች ቡና ማጣጫ ሊጠቅም ይበጅ እንደሁ እንጂ ሃገራዊ ጥቅም የለውም። ሃገር በአሉባልታ አትገነባም። " ጦር ከፈታው፣ ወሬ የፈታው " እንዲሉ። ተስፋዬ በለመደበትና ባደገበት ብእሩም በሚመጥነው ደረጃ ቢናገርም፣ ቢጽፍም ባልከፋ ነበር። ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ጠቃሚ ሀሳብ ማፍለቅ ከሰከነ አይምሮና ከተባ ብእር አንጀት ይወለዳል። የተማረ ሁሉ አያነበንብም፣ ያነበነበ ሁሉ አያዜምም፣ ያዜመ ሁሉ ደግሞ ቅኔ አይዘርፍም። አንዳንዶች መንታ ልብና መንታ እግር ስለአላቸው የሁለት ዓለም ሠራዊት በአንዴ ማዝመት ያምራቸዋል።

በዚህ ዘመን በኢትዮጵያ ታሪክና ሕዝብ ላይ አረም የበዛበት ዘር ለማብቀል የሚፍጨረጨሩ በርካታ ጸሃፊዎች እንደአሸን እየፈሉ በአሉበት በአሁኑ ወቅት እንኳ፣ እንዲህ በገሀድ ፍጥጥ ያለ፣ ፈሩን የሳተና የተዛባ የሐሳብና የቃላት ትርጉም ደራሲ አላጋጠመኝም። የሁለት ዓለም ወግ ባንድ ምላስ ማስተናገድ ይቻል ይሆን ? በተዛባ እውቀትና ትርጉም፣ አለያም በስውር ተልእኮ፣ እንዲያም ሲል ከመሰሪነት በሚመነጭ ሀሳብ የሌሎችን ቀልብ ለማደፍረስ ከንቱ ቅኝት መቃኘት ነው የሚሆነው። እሱ ደግሞ መጨረሻው ቅሌት ነው የሚያተርፈው። የአሉሽ አሉሽ ወግ እንኳን ሀገር የግል ቤት አይገነባም። ወግ መጠረቅ ወይም መጻፍ፣ ታሪክን ከመቃኘትና ከመከተብ ጋር እጅግ የተራራቁ ግብሮች ናቸው።

ከተስፋዬ ጽሁፍች ብዙ ታዝበናል፣ አዝነናል ስቀናልም። አንዳንዶቻችን ገና ከጅምሩ መዳረሻቸው ለመቃኘት ችለናል። የሱንም ማንነት ለማወቅም ቢሆን ብዙ ማጣቀሻ አላስፈለገንም። ራሱን በዛው በጀመረው የወግ ጥረቃ (በተልእኮም ይሁን በግል አቋም) ዙሪያ ገድቦ ቢጫወት የሚያዋጣው ይመስለኛል።

ምክንያቱም አቶ ተስፋዬ ከምድር በላይ ሊያሳየን የሚሞክረው የጥላቻ ዛፍ ከምድር ውስጥ ከብዙ ከምንወዳቸው ዛፎች ጋር በሥሮቹ አማካኝነት ተጋምዶና ተጠላልፎ እየኖረ ስለመሆኑ አስቦ የሚያውቅ አይመስለኝም። የቡርቃ ዝምታ ሊቀጥል የማይገባው ለሕዝብና ለሃገር የማይጠቅም የባዕድ ተልእኮ ነውና ።

ለማንኛውን በአንድ አባባል ዛሬን ላክትም ።

አንድ ደሃ ገበሬ ሚስቱ ትሞትበትና የሚያለብሳት ግምጃ አጥቶ ተቸግሮ ሳለ አንድ ጎረቤት ይህንን ተመልክቶ ከቤቱ ግምጃ አውጥቶ ይሰጠዋል።ገበሬው የተዋሰውን ግምጃ አስከሬኑን አልብሶ በበቅሎ ጭኖ ሲጓዝ ምንም እንደነካት ሳይታወቅ በቅሎዋ ትደነብርና ታመልጣለች። ይኼን ጊዜ ያ ደሃ ገበሬ በጣም አዝኖ እንዲህ ብሎ ገጠመ ይባላል ።

"የማታውቅበትን የሰው ግምጃ ለብሳ፣
ተመለሽስ ቢሏት ወዴት ተመልሳ።"

ይቀጥላል።

ተስፋዬ በአሁኑ ወቅት አንገብጋቢውን ጥያቄ መመለስ ሲያቅተው በሕይወት የማይገኙ ግለሰቦች እየጠቀሰ የተሳሳተ መረጃ ከሰጠ እኔም ባልሆን ሌሎች የሚታዘቡ ይቀጥሉታል።

ስለ ሃገራችን የሚያስቡ ሁሉ ሰላም ይከረሙ!

Beljig.ali@gmail.com

ኅዳር / 2004 ጀርመን